# የግንቦት 7 ድምጽ

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 100 ሚያዝያ 7 2002 ዓ.ም


ምርጫን እንደመሰለያ መሳሪያ የሚጠቀመው ወያኔ በድህረ ምርጫ 97 በህዝባችን ላይ የፈጸመው አይነት ፋሽስታዊ ጭፍጨፋ እንዳይደገም ከተፈለገ ነጻ እና ገለልተኛ የሆነ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት፤ ለሁሉም እኩል የሚያገለግል የሚዲያ አገልግሎት፤ ታማኝነታቸው ለህገመንግሥቱ ብቻ የሆነና ከፖለቲካ ወገናዊነት የጸዱ የፖሊስ፤ የመከላኪያና የደህንነት ተቋማት መመስረት ይኖርበታል።

ለወያኔ እድሜ መራዘሚያ ህጋዊና ሞራላዊ መሰረት እንዲያስገኝ ታስቦ በሚካሄድ ምርጫ መሳተፍ ለህዝባችን የሚያስገኘው ፋይዳ አይኖርም!!!

## በሳተላይት አማካኝነት ወደ ኢትዮጵያ የሚተላለፍ የመጀመርያ ነጻ ቴሌቭዥን ጣብያ መመስረቱ ይፋ ሆነ

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት (ወይም በምህጻረ ቃል ኢሳቴ) በመባል የሚታወቀው ድርጅት ባወጣው መግለጫ ከዚህ ወር አጋማሽ አካባቢ ጀምሮ ወደ ኢትዮጵያና የተቀሩት የአለማችን ክፍላት የሚያደርገውን ስርጭት እንደሚጀምር ገልጿል።

ድርጅቱን ያቋቋሙት አካላት ኢትዮጵያ እና ህዝቧ አሁን ወዳሉበት አስቸጋሪ እና ውስብስብ ችግሮች እንዲደርሱ ካደረጓቸው ምክንያቶች አንዱና ዋናው የመረጃ እጥረት እንደሆነ እንደሚያምኑና፤ የቴሌቪዥን ድርጅቱም የህዝብ አይንና ጆሮ የሆነ የመገናኛ ብዙሃን በመሆን፤ አስተማማኝ፣ ነጻና ገለልተኛ መረጃዎችን በማቅረብ፤ ለችግሮቻችን መፍትሄ ለመፈለግ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የራሱን አስተዋጾ ለማድረግ ዝግጁ ሆኖ የቀረበ መሆኑን መግለጫው አሳውቋል።

ድርጅቱ ያወጣውን መግለጫ ሙሉ ቃል በገጽ 4 ይመልከቱ።

## “ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ሕገ-ወጥና አምባገነናዊ በሆነው የወያኔ ስርአት ስር ከቶውኑ ሊከናወን አይችልም” ሲሉ ዘጠኝ የተቃዋሚ ድርጅቶች የጋራ መግለጫ አወጡ

ዘጠኝ የኢትዮጵያ ተቃዋሚ ድርጅቶች መጪውን የምርጫ ተውኔት በመቃወም የጋራ መግለጫ አውጥተዋል። ሚያዝያ 1፣ 2002 አመተ ምህረት ለዝግጅት ክፍላችን የደረሰው መግለጫ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ እና ተቃዋሚዎች ከ1997ቱ ምርጫ መጭበርበር የተማሩት አብይ ትምህርት፣ ነፃና ገለልተኛ መንግስታዊ ተቋማት መደራጀት እንዳለባቸው ነው ይላል።

መግለጫውን የሰጡት ድርጅቶች፡- የኢትዮጵያ ህዝብ አርበኞች ግንባር፤ የቤንሻንጉል ህዝብ ንቅናቄ፤ የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ፤ የአማራ ዴሞክራሲያዊ ሃይል ንቅናቄ፤ ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነት እና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ የኢትዮጵያ ህዝቦች የፍትህና እኩልነት ግንባር፤ የአፋር ህዝብ ፓርቲ፤ የጋምቤላ ህዝብ ነፃነት ንቅናቄ፤ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነት የፍትህ ንቅናቄ ናቸው።

(ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## አምባገነን መለስ ባለቤት አዜብ መስፍን በግለሰቦች ላይ የምታደርገውን ህገ-ወጥ ጫና እንደቀጠለች መሆኑ ታወቀ

የግንቦት 7 ዘጋቢ ከአዲስ አበባ ታማኝ ምንጮችን በመጥቀስ በላከው መረጃ፥ አዜብ መስፍን ከአያት የመኖሪያ ቤቶች ስራ ድርጅት ባለቤቶች ውስጥ አንዱን ወይ በንግዱ ውስጥ እንዲያስገባት፤ ወይም የፓርቲ አባል እንዲሆን ነግራው እንደነበር እና ግለሰቡ ፈቃደኛ እንዳልነበረ ለማወቅ ተችሏል። ግለሰቡ ግብር አልከፈለም በሚል ክስ መታሰሩ እና መከሰሱ ይታወቃል።

የመለስ ዜናዊ ባለቤት አዜብ መስፍን ጫት ወደ ውጭ አገር ከመላክ ጀምሮ በበርካታ የንግድ ዘርፎች እንደምትሳተፍ የሚታወቅ ሲሆን፤ በህገ-ወጥነቱ ከሌሎቹ ለየት ባለ ሁኔታ አይን አውጣ የሆነው የንግድ አሰራሯ እንደ ስብሃት ነጋ ባሉ ሌሎች የወያኔ ባለስልጣናት ዘንድ “እኛንም ታጋልጠናለች” የሚል ስጋት እና መቃቃር ፈጥሮ እንደነበር አንዳንድ ምንጮች ይገልጻሉ። በርካታ የወያኔ ሚስጥሮችን “የጋዜጠኛው ማስታወሻ” በሚል መጽሃፉ ያጋለጠውና የቀድሞ የወያኔ የፕሬስ ጽህፈት ቤት ሃላፊ ተስፋዬ ገብረአብ በዚሁ መጽሃፉ፤ አዜብ መስፍን ጫት አልሸጥ ባሏት የሃረር ገበሬዎች ላይ የወያኔን ጦር እስከማዝመት የደረሰች እንደሆነች መጻፉ ይታወሳል።

ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በጥቂት ሰዎች ቁጥጥር ስር ለማዋል ሲያደርግ በቆየው ጥረት፣ የፓርቲ አባል ለመሆን ወይም ከወያኔ ባለስልጣናት ጋር በሽርክና ለመስራት ፈቃደኛ ያልሆኑ ዜጎችን በተለያዩ ክሶች እየወነጀለ ማሰር፣ እንዲሰደዱና ንብረታቸውን እንዲያጡ ማድረግ የለመደው አሰራር እንደሆነ ይታወቃል። የአያት የመኖሪያ ቤቶች ስራ ድርጅት ባለቤት እንግልትም ከዚህ ጋር የተያያዘ ሳይሆን እንደማይቀር የሪፖርተራችን ምንጭ ገልጸዋል።

### ግዜ

## ኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ በሚል ርእስ የተዘጋጀው ኮንፈረንስ በዋሽንግተን ዲሲ ተካሄደ

ከሚያዝያ 1 እስከ ሚያዚያ 3፣ 2002 አመተ ምህረት ኢትዮጵያና የአፍሪካን ቀንድ በተመለከተ በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት የሚደረግበት ኮንፈረንስ በዋሽንግተን ዲሲ በስኬት መካሄዱን ሪፖርተራችን ከስፍራው ባስተላለፈው ዘገባ ገልጿል።

ኢትዮጵያውያንና የሌሎች አገር ዜጎች የሆኑ ምሁራን፣ ታዋቂ ግለሰቦች እና የቀድሞ የመንግስት ባለስልጣናት እና አማካሪዎች ተገኝተው ንግግር ያደረጉበት ይህ ስብሰባ፤ በርካታ ታዳሚዎች እንደነበሩት እና ገንቢ ውይይቶች እንደተካሄዱ ሪፖርተራችን ገልጿል። ይህ ስብሰባ የተለያዩ አመለካከቶች እንዲገለጹበት ሆኖ የተዘጋጀ እና የወያኔው አገዛዝ ተወካዮች ሳይቀሩ ተገኝተው ሃሳባቸውን እንዲገልጹ የተጋበዙበት ቢሆንም፣ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ግን ክፉኛ ሲቃወመው መሰንበቱ ይታወቃል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ወያኔ በመጪው የምርጫ ተውኔት ማሸነፉን አስቀድሞ እንደወሰነ ማሳየቱን ቀጥሏል

በምርጫ ዘጠና ሰባት የዴሞክራሲን በር ገርበብ አድርጎ ሲከፍት በህዝብ መተፋቱን ያረጋገጠው ወያኔ፣ ያንን ስህተት ዳግም ላለመስራት የሚያካሂደውን ሩጫ ቀጥሏል። ሰሞኑን እንደ ደረሰን መረጃ ከሆነ በሰሜን አሜሪካ የሚገኙ የወያኔ ደጋፊዎች እንኳ ከወዲሁ የወያኔን የምርጫ ድል ለማክበር ለነሃሴ ወር ቀን ቆርጠው ዝግጅት ጀምረዋል።

ባለፈው ሳምንት ሃሙስ የወያኔው ምክትል ዋሾ በረከት ስምኦን ለጋዜጠኞች በሰጠው ገለጻ ደግሞ መድረክ የተባለው የፓርቲዎች ስብስብ ወንጀል እየፈጸመ መሆኑን ተናግሯል። እንደ ምክትል ዋሾ በረከት ስምኦን ገለፃ፥ በትግራይ ክልል የመድረክ እጩ የሆኑት አቶ አረጋዊ ገብረዮሃንስ የተገደሉት በግል ጸብ እንጂ በወያኔ አይደለም የሚለውን የአገዛዙን ውሸት የማይቀበል፣ ከህግ ያፈነገጠ ወንጀለኛ ነው።

በጉዳዩ ላይ አስተያየት የሰጡን ግለሰቦች፣ ይህ ወያኔ ከምርጫው በፊት ወይም በኋላ የተወሰኑትን ተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች ለማሰር እና የጉልበት አሸናፊነቱን ለማረጋገጥ የሚያደርገው ዝግጅት አካል ነው ብለዋል።

## የህዝቡን ቁጣ መቋቋም አቅቶት የተፈረካከሰው የኪርጊስታኑ መንግስት ሁኔታ ለኢትዮጵያም ምሳሌ ይሆናል ተባለ

ባለፈው ሳምንት እሮብ የተቀጣጠለው እና እንደ አንድ ታዋቂ የዜና አውታር አገላለጽ ባጭር ጊዜ ውስጥ የአምባገነኖች ቅዠት የሆነው የኪርጊስታን ህዝብ ቁጣ አምስት ቀናት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የፕሬዚደንት ኩርማንቤክ ባኪዬቭን አገዛዝ ፈረካክሶ ጥሎታል። የአገዛዙን ስር የሰደደ ሙስና እና ሊቆጣጠረው ያልቻለውን የዋጋ ንረት በመቃወም ሰልፍ የወጡትን በሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች ክፉኛ እቀጣለሁ ብሎ ሲፎክር የነበረው ፕሬዚደንት ኩርማንቤክ እግሬ አውጪኝ ብሎ በሽሽት ላይ ይገኛል።

በሰላማዊ ሰልፈኞች ላይ ያለማስጠንቀቂያ ተኩስ የከፈቱት ወታደሮች እና ፖሊሶች 75 ሰዎች ገድለው 400 ቢያቆስሉም፤ ህዝብ የተፋውን አገዛዝ ግን ሊያድኑት አልቻሉም።

የኩርማንቤክ ባክዬቭ መንግስት እራሱም አምባገነናዊ መንግስት ገልብጦ ሁኔታዎችን አሻሽላለሁ በሚል ከአምስት አመታት በፊት ስልጣን ላይ የወጣ ቢሆንም፤ በፍትህ እና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ መንግስት በማቋቋም ፈንታ ስልጣንን በፕሬዘንደንቱና በጥቂት ዘመድ እና ጓደኞቹ ሙሉ በሙሉ ቁጥጥር ስር በማድረጉና የኪርጊስታንን ህዝብ ድህነት ባባባሰ ሙስና ውስጥ በመዘፈቁ በህዝብ ለመተፋት በቅቷል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት በሙስሊሞች ላይ አፋኝ ውሳኔዎች ማስተላለፉ ታወቀ

የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ሰሞኑን በጠራው ልዩ ስብሰባ የሙስሊም ዜጎችን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ በሚመለከት አፋኝ ውሳኔዎችን ማስተላለፉን የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከው መረጃ አሳውቋል።

ምክር ቤቱ፥ ሙስሊሞች ያለ ምክር ቤቱ እውቀት የሚደረጉ ማንኛውንም አይነት ስብሰባ እንዳይሳተፉ፤ እንዲሁም ለማንኛውም ፖለቲካዊ ጉዳይ የገንዘብ ድጋፍ እንዳይሰጡ የሚሉ ውሳኔዎችን ማስተላለፉ ታውቋል።

ዘጋቢያችን በጉዳዩ ላይ ያነጋገራቸው አንዳንድ ሙስሊም ዜጎችም፣ ይህ ውሳኔ ተፈጥሯዊ መብታቸውን የሚጋፋ እና ምክር ቤቱ ለአምባገነናዊው አገዛዝ ያለውን አድሎ የሚያሳይ ነው ብለዋል። በተጨማሪም፥ ይህ ሙስሊም ኢትዮጵያውያን በፖለቲካው ውስጥ በመሳተፍ ዜግነታዊ ግዴታቸውን (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## እየተዋጋን ያለው ዘረኝነት ይኸ ነው!

"አይጋ ፎረም" የተባለው ድረ-ገጽ የመለስ ዜናዊና ስብሃት ነጋ የዳያስፖራ ልሳናቸው መሆኑ ይታወቃል። ሰሞኑን በዚሁ ድረገፅ ላይ "መጥፎ ታሪክን ላለመድገም መጠንቀቅ" በሚል ርዕስ ተንሱ የማነብርሃን በተባለ ጸሃፊ ስም በትግርኛ የተፃፈው ጽሁፍ የወያኔን በተለይም የመለስንና ስብሃትን ጽንፍ የረገጠ ዘረኛ አስተሳሰብ በማያሻማ አገላለጽ ግልጽ አድርጎ አቅርቦልናል።

ወያኔ ውጥረት ውስጥ ሲገባ እንዲህ ዓይነት ጽሁፎችን በመበተን የትግራይን ማኅበረሰብ ስጋት ውስጥ በመክተት በማምለጫነትና ድጋፍ ማሰባሰቢያነት እንደሚጠቀምባቸው ገና ከበረሃ ጊዜው ጀምሮ ተደጋግሞ የተስተዋለ ጉዳይ ነው። በምርጫ 97 ማግሥት መምህር ገብረኪዳን ደስታ የተባለ የታሪክ ፀሃፊ ነኝ ባይ "የትግራይ ሕዝብና የትምክህተኞች ሴራ ከትናንት እስከ ዛሬ" በሚል ርዕስ ባሳተመው መጽሃፍ አማራን ትምክህተኛ ግን ፈሪ፤ ትግራዋይ ደግሞ ጀግናና ታጋሽ እንደሆነ ጽፏል። የዚያ መጽሃፍ ዋነኛ ዓላማ የትግራይን ሕዝብ በአማራው ላይ ማነሳሳት እና ሕዝብን ከሕዝብ ማናቆር እንደሆነ የመጽሃፉን ጥቂት ገፆች ያገላበጠ አንባቢ ይገነዘባል። እንዲህ ዓይነቱ ከፋፋይና መርዘኛ መጽሃፍ በአዲስ አበባ ሌሎች አካባቢዎች በግላጭ እየተሸጠ በነበረበት ወቅት ነው - የአባዬን በእምዬ ማላከክ እንዲሉ - በሰላማዊ ምርጫ የተሳተፉ የቅንጅት መሪዎች በዘር ማጥፋት ወንጀል ሙከራ ተከሰው ቃሊቲ እስር ቤት ይማቅቁ የነበረው።

እነዚህ ወቅት እየጠበቁ በተለያዩ ሰዎችና የብእር ስሞች እየተፃፉ የሚወጡ እጅግ መርዛማና አደገኛ ጽሁፎችን ንቆ መተው የሚገባ ቢሆንም አንዳንዴ ለታዛቢ እይታ ማቅረብ ተገቢ ነው ብለን እናምናለን። በእነዚህ ጽሁፎች አማካይነት የመለስ-ስብሃት አገዛዝ በምን አይነት የዘረኝነት አስተሳሰብ እንደተወጠረና የገባበትን ሁዋላ ቀር መንደርተኛ አካሄድ እንድንረዳ አጋዥ ይሆናል። ከዚህ አንፃር ነው ሰሞኑን "በአይጋ ፎረም" ላይ ወጥቶ የሚገኘውን መርዘኛ ጽሁፍ ልንተችበት የፈቀድነው።

ይህ መርዘኛ ጽሁፍ የኢትዮጵያን ታሪክ የአማራና የትግራዋይ የፍልሚያ ታሪክ አድርጎ በማቅረብ ይቀባጥራል። በዚህ ፍልሚያ ውስጥ ትግራዋይ በጠቅላላ ጀግና፤ ተበዳይና ተጨቋኝ፤ በተቃራኒው አማራው በጠቅላላ መሰሪና ጨቋኝ ተደርጎ ተስሏል። ትግራዋይ "ወገን" ሲሆን፤ አማራው ደግሞ "ጠላት" ሆኖ ቀርቧል። የሚገርመው የትግራዋዩ ወገን ከመሳፍንት አልፎ በንጉሥ እየተመራም ቢሆን በጽሁፉ አገላለጽ ተጠቂነቱና ተበዳይነቱ አይቀርም። ትግራይ ሁሌ እንደተበደለ፤ አማራ ሁሌ እንደበደለ ነው። ከአማራና ትግራዋይ ሌላ ምንም ሌላ ዘውግ (ብሄር፣ ብሄረሰብ) የለም። ኢትዮጵያ ማለት ሁለቱ ናቸው። የኢትዮጵያ ታሪክ ማለት ደግሞ የሁለቱ ፍትጊያ ማለት ነው።

የጽሁፉ አቅራቢ "የታሪክ ትንተናውን" በመቀጠል ከ1881-1889 ዓ.ም. ባለው ወቅት የትግራይ መሳፍንት በመከፋፈላቸው፤ አፄ ዮሃንስም የትግራይን ሕዝብ በተገቢው መጠን "ከጎናቸው ባለማሰለፋቸው" ኃይላቸው ተበታትኖ በተንኮለኞቹ አማሮች እጅ መውደቃቸውን ይገልጻል። በመሳፍንት መካከል ሽኩቻ መኖር ልዩ የሆነ የትግራይ እውነታ የሆነ ይመስል የትግራይ መሳፍንት ተባብረው በመቆም አማራን መመከት ባለመቻላቸው አጥብቆ ይኮንናቸዋል። "ማየት ለፈለገ ሚኒሊክ የጨፈጨፋቸው ትግራዋይ አጥንት አሁንም በየተራራሮች አናት ላይ ይገኛል" በማለት ጥላቻን ለማስረጽ ይተጋል።

የትግራይ መደፈር ያንገበገባቸው "ብርቅየ ልጆች" በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወደ በረሃ እንደገቡና የትግራይንም ክብር እንደመለሱ በማብሰር የወያኔን ዓላማ ምንነት በማያሻማ ቋንቋ ይገልፃል። ይሁንና ይህ የወያኔ ተጋድሎ ገና በጥልቀት አልተወራም፤ መወደስ የነበረትን ያህልም አልተወደሰም እያለ ምሬቱን ይገልጻል።

ጽሁፉ በአፄ ዮሃንስ ዘመነ መንግሥት በመሳፍንቱ ውስጥ በነበረው ሽኩቻ ምክንያት ትግራይ እንደተዳከመች ሁሉ አሁንም በወያኔ ውስጥ በሚፈጠረው ሽኩቻ ምክንያት ተመሳሳይ መዳከም እንዳይመጣ ያለውን ስጋት አስረግጦ ይገልፃል። አረጋዊ በርሄን፣ ስዬ አብርሃን፣ ገብሩ አስራትንና አሰገደ ገብረስላሴን በስም እየጠራ በከሃዲነት ይኮንናቸዋል። ከላይ ስማቸው የተጠቀሱትን ግለሰቦች የአማራ በተለይም የሸዋ አማራ ተላላኪዎች ሆነዋል በማለት የትግራይ ሕዝብ እነዚህን ሰዎች በጠላትነት እንዲፈርጅ እጅግ በጣም ስሜታዊ በሆነ መንገድ ይቀሰቅሳል።

ይህ ነው የወያኔ ርዕዮተ ዓለም!!! ይህ ነው የመለስ ዜናዊ እና የስብሃት ነጋ እውነተኛ ማንነት። ይህ ነው ያፈጠጠ ያገጠጠ ዘረኝነት። በዚህ አስተሳሰብ ውስጥ አንዳችም የእርቅ መንፈስ የለም። በዚህ አስተሳሰብ ውስጥ አንዳችም የጋራ ጥቅም የለም። በዚህ አስተሳሰብ ውስጥ አንዳችም የአብሮነት መንፈስ የለም።

ይህ መርዘኛ አስተሳሰብ በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ላይ ብቻ ያለ አይደለም። "በአብዮታዊ ዲሞክራሲ" እና "ልማታዊ መንግሥት" መዝሙሮች ተጀቡኖ የመለስ መንግሥት ፓሊሲ ሆኖ ተግባራዊ እየተደረገ ነው። ይህን ያነበበ ሰው መለስ መቀሌ ላይ "ጠላቶቻችን" ሲል እነማንን ማለቱ እንደሆነ ግልጽ ይሆንለታል።

ይህ ዘረኛ አስተሳሰብ እና ከሱም የተቀዳው ፓሊሲ ሁላችንንም እየጎዳ፤ አገራችንንም እየገደለ ይገኛል። ይህ አስተሳሰብ በዓለማችን ውስጥ በየትኛውም ቦታ ቢሆን እንዲኖር እድል ሊሰጠው የማይገባ ነው።

ልጆቹ የወደቁለት ዓላማ በዚህ መንገድ ሲገለጽ መስማት ለትግራይ ሕዝብ ምን ያህል ቁስል እንደሆነ ይሰማናል። ለወያኔ እኩይ ዓላማ ሲሉ ልጆቻቸውን ያጡ ወላጆች ህመማቸው ያመናል። ወላጆችም ልጆችም የሚያውቁት ለነፃነትና ለፍትህ እንደተዋጉ ነበር፤ አዋጊዎቹ ግን ገና ከመነሻው ምን ዓልመውና ተልመው እንደተነሱ እነሆ ያለአንዳች እፍረት እየነገሩን ነው።

ግንቦት7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ እያጋለጠ ያለው ይህንን ሥር የሰደደ እና እጅግ ኋላቀር የሆነ ዘረኝነትን ነው። ለይሉኝታና ለአብሮነታችን ስንል እንደብቀው ብንል እንኳ አልደበቅ፣ አልከለል ያለ እውነት ሆኖብናል።

ወያኔ ሊሻሻል ስለማይችል መወገድ ያለበት ኃይል ነው የምንለውም ለዚህ ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

**ውድቀት ለዘረኞች!!!!!**

## ኢትዮጵያና የአፍሪካ ቀንድ በሚል ርእስ . . . ከገጽ 1 የዞረ

በስብሰባው ላይ ለውይይት ፕሮግራሙ ከተገኙት እንግዶች ውስጥ የግንቦት 7 ንቅናቄ ሊቀመንበር ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ የሚገኙበት ሲሆን፤ ለፕሮግራሙ ተሳታፊዎች ጽሁፍ ያቀረቡ መሆኑም ታውቋል። በተጨማሪም፥ የግንቦት 7 ንቅናቄ የውጭ ጉዳይ ሃላፊ አቶ ኤፍሬም ማዴቦ በዋሽንግተን ዲሲ ተገኝተው ንግግር ማድረጋቸውን ከዝግጅቱ ፕሮግራም ለማወቅ ተችሏል።

ሪፖርተራችን ያናገራቸው አንድ ግለሰብ፥ "ስብሰባው ነፃ እና ገለልተኛ በሆነ መንገድ የተለያዩ ሃሳቦች እንዲቀርቡ እና ግልጽ በሆነ መንገድ ስለሃገራችን እንድንወያይ ከማስቻሉ አኳያ ሊመሰገን እና አዘጋጆቹም ሊበረታቱ ይገባል፤ ይህንን አይነት ዝግጅት በአገራችንም የምናደርግበት ጊዜ ይናፍቀኛል" ያሉ ሲሆን፤ "በዝግጅቱ ላይ የተገኙ የሌሎች አገሮች ዜጎችም ስላሉ ተብሎ ስብሰባው በእንግሊዝኛ መካሄዱ ግን፣ ብዙ ሰዎች በውይይቱ ላይ በሙሉ ልብ የመሳተፍ እድላቸውን የቀነሰባቸው መስሎ ተሰማኝ" ሲሉ አስተያየታቸውን ገልጸዋል።

## "ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ሕገ-ወጥና አምባገነናዊ . . . ከገጽ 1 የዞረ

ተቃዋሚ ድርጅቶቹ በመግለጫቸው፥ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ እንዲደረግ፦ ከወያኔ ድርጅትና ወደፊትም ቢሆን ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ጉዳይ አስፈጻሚነት ነፃ የሆነ የመከላከያ፣ የደህንነትና የፖሊስ ሃይል፤ ነፃ የፍትህ ስርአት፤ ነፃ የምርጫ አስፈፃሚ ቦርድ፤ እንዲሁም ነጻ ሚድያ በቅድሚያ መሟላት እንዳለባቸው ገልጸዋል። እነዚህ ተቋማት ባግባቡ ባልተደራጁበት የወቅቱ ሁኔታ ግን ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ማካሄድ የማይታሰብ መሆኑን የኢትዮጵያ ህዝብ ከሊቅ እስከ ደቂቅ ያውቀዋል ብለዋል።

እነዚህ ዘጠኙ ድርጅቶች ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ የአገራችንን የተወሳሰቡ ችግሮች መፍቻ ዋነኛው መሳሪያ ነው ብለው እንደሚያምኑ፥ ነገር ግን ያ ወያኔ በየጊዜው በሚያዘጋጀው የፌዝ ምርጫ በመሳተፍ እውን ሊሆን እንደማይችል ገልጸዋል።

## የህዝቡን ቁጣ መቋቋም አቅቶት የተፈረካከሰው . . . ከገጽ 1 የዞረ

የባኪየቭ መንግስት ምንም እንኳ ሙስናውን እና የሰብአዊ መብት ረገጣውን እያየች የገንዘብ ድጋፍ ትሰጠው በነበረችው የአሜሪካ መንግስት የተደገፈ ቢሆንም፤ ይህም ቢሆን ከህዝብ ቁጣ ሊያድነው አልቻለም። ይህም ብቻ ሳይሆን፤ ከጥቅማቸው እንጂ ከአምባገነኖቹ ጉዳይ የሌላቸው ሃያላን አገራት ባኪየቭን ረስተው አዲስ ከተመሰረተው የተቃዋሚዎች መንግስት ጋር መስራት ጀምረዋል።

የወደቀው የኪርጊስታን መንግስት በኢትዮጵያ ካለው የወያኔ አገዛዝ ጋር ብዙ ተመሳሳይነት አለው የሚል መልክት የላኩልን የቨርጂኒያ ነዋሪ አቶ ሙሉአለም ቸኮል፤ የውጭ አገራት ጫና ባይኖር እንኳ ህዝቡ በቃኝ ሲል ወያኔ መፈንዳቱ የማይቀርም ቅርብም ነው ብለዋል። ስግብግብነት፣ ጎጠኛነት፣ ስር የሰደደ ሙስና፣ የዋጋ ንረትና የድህነት መንሰራፋት የኪርጊስታንን እና የኢትዮጵያን ሁኔታ ያመሳስሉታቸዋል የሚሉት እኚሁ አስተያየት ሰጪ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ የኪርጊስታንን ህዝብ ቆራጥነት እንደ ምሳሌ ወስዶ "በቃኝ!" ሊል ይገባዋል ብለዋል።

የሳንፍራንሲስኮ ክሮኒክልን ያነጋገሩ ኢሽንቤክ አሺሮቭ የተባሉ የሃምሳ አመት ኪርጊስታናዊ መምህር፥ "ብንራብም እኛ ኩሩ ህዝብ ነን፤ መቶም ቢሆን ወደ ኋላ አንልም" ብለዋል።

በግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

ሃይለ ሀሳብ

የግንቦት 7 ድምጽ፤ ቁጥር 100 ሚያዝያ 7 2002 ዓ.ም፤ ገጽ.3

# ወደፊት መራመድ እንዴት አቃተን? ለወደፊቱስ ምን ማድረግ እንችላለን?

ዶ/ር ታደሰ ብሩ (ማርች 27 ቀን 2010 ኦስሎ፣ ኖርዌይ በተካሄደ ህዝባዊ ስብሰባ ላይ ያቀረቡት ጽሁፍ) **ክፍል 1**

## ክቡራትና ክቡራን

በዚህ መድረክ ላይ ተገኝቼ ሃሳቤን የማካፈል እድል በማግኘቴ የተሰማኝን ደስታ እገልፃለሁ። ለተሰጠኝ እድልም ምሥጋናዬ ወሰን የለውም። ዛሬ ለመናገር የደፈርኩት ወደፊት መራመድ እንዴት አቃተን? ለወደፊቱስ ምን ማድረግ እንችላለን? በሚል ርዕስ ሲሆን ጉዳዩ ከርዕሱ ጀምሮ አወዛጋቢ ሊሆን እንደሚችል አውቃለሁ። ጥያቄውን መመለስ ደግሞ ከዚያ የባሰ ከባድ ነገር ነው ። እኔም ለዚህ ጥያቄ አጥጋቢ ምላሽ አለኝ ለማለት አልደፍርም። ይሁን እንጂ በዚህ ጉዳይ ላይ የመሰለኝን ሃሳብ ባቀርብ ለውይይት መነሻ ይሆናል በሚል ተስፋ ተበረታትቼ ቀርቤዓለሁ። ሆኖም እንዲህ ዓይነት ጭንቅላት የሚያዞርን ጥያቄ በቀልድና በምሳሌ ካላዋዙት አይሆንምና አቀራረቤን ከተለመደ የስብሰባ ንግግር ለየት ያለ እንዲሆን አድርጌዓለሁ። ሳትጨነቁ እየተዝናናችሁ ትሰሙኛላችሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። በንግግሬ መጨረሻ ራሳችንን መታዘቢያ ጥቂት ነጥቦችን መወርወር ከቻልኩ ዓላማዬን አሳክቻለሁ ብዬ አስባለሁ።

## ክቡራትና ክቡራን

ከቅርብ ጊዜ ታሪካችን ውስጥ ሶስት አስርት ዓመታትን በሃሳባችሁ ቃኙልኝ። 1950ዎቹ፣ 1970ዎቹ እና አሁን ያለንበት የ1990ዎቹ መጨረሻና 2000ዎቹ መጀመሪያ።

በ1950ቹ የአክሊሉ ሃብተ ወልድ ካቢኔ ኢትዮጵያ በፈጣን እድገት ላይ መሆኗ ማስረጃ እያጣቀሰ መግለጫ ይሰጥ ነበር። በ1970ዎቹ ኢትዮጵያ በፈጣን ግስጋሴ ላይ መሆኗን የመንግሥቱ ኃ/ማርያም መንግሥት ማስረጃዎችን እያጣቀሰ ያብራራ ነበር። አሁን በ2000ዎቹ የመለስ ዜናዊ መንግሥት ስለኢትዮጵያ ግስጋሴ በማስረጃ ጋጋታ እያደናገረን ነው። እንዴት ነው ስንገሰግስ ከርመን አንዳች ቦታ እማንደርሰው?

በ1950ቹ ኢትዮጵያ ድህነትን ስትዋጋ ነበር፤ በ70ዎቹ ኢትዮጵያ ድህነትን ስትዋጋ ነበር፤ አሁንም በ2000ም ኢትዮጵያ ድህነትን እየተዋጋች ነው። ድህነት በተዋጉት መጠን የሚፋፋ ነገር ነው እንዴ?

በ50ዎቹ የኢትዮጵያን ኋላቀር ግብርናን ከመሠረቱ ለመቀየር የግብርና ኤክስቴንሽን መርሃግብር ተነድፎ፤ ሥራ ላይ ውሎ ውጤታማ እንደነበር በጊዜው የወጡት የመንግሥት መግለጫዎች ያስረዳሉ። በ70ዎቹ የኢትዮጵያን ኋላቀር ግብርናን ከመሠረቱ ለመቀየር የመንደር ምሥረታ መርሃግብር ተነድፎ፤ ሥራ ላይ ውሎ ውጤታማ እንደነበር በወቅቱ የወጡ የመንግሥት መግለጫዎች ያስረዳሉ። ዛሬም የኢትዮጵያን ኋላቀር ግብርናን ከመሠረቱ ለመቀየር የግብርና ኤክስቴንሽን መርሃግብር ተነድፎ ሥራ ላይ እየዋለ ነው፤ ውጤታማነቱም ሚሊየነር የሆኑ ገበሬዎች በቴሌቪዥን እየነገሩን ነው። አንድ ነገር ስንቴ ነው ከመሠረቱ የሚቀየረው? እንዴት ነው ግብርናችን ከመሠረቱ ከተቀየረ በኋላ እንደገና ተመልሶ ኋላ ቀር የሚሆነው?

በ50ዎቹ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደራሲዎቹን እንዲመርጥ በመፍቀድ ፀሃዩ ንጉሥ ለኢትዮጵያ ፀሃይ አወጡላት፤ ለመጀመሪያ ጊዜ ዲሞክራሲን ሥራ አዋሉ። በ1970ዎቹ ለመጀመሪያ ጊዜ ጭቁኖች በፓርቲያቸው ኢሠፓ አማካይት የሥልጣን ባለቤት በመሆናቸው እውነተኛው ዲሞክራሲ ተግባራዊ ሆነ፤ በምሥራቅ አፍሪካ ጎህ ቀደደ ተባለ። በቅርቡ ለመጀመሪያ ጊዜ ብሄር ብሄረሰቦች በፈቃዳቸው ተደራድረው ኢትዮጵያ የምትባል አገር መሠረቱ ተባለ። ይህች አገር ለመጀመሪያ ጊዜ ዲሞክራሲን እየተለማመደች ነው ይባላል። ሁሌም ለመጀመሪያ ጊዜ መሆኑ ልብ ይሏል።

በ50ዎቹ ንጉሡ ሕዝባቸውን ከማይምነት ነፃ ለማውጣት የፊደል ሠራዊትን አዘመቱ። በ70ዎቹ የተማረ ሁሉ ያስተምር ያልተማረ ሁሉ ይማር ተባለ። በ2000ም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ማዳረስ ግባችን ነው ተባለ። ምንድነው ነገሩ? እንዲህ ዓይነት ነገሮችን እንዘርዝር ብንል ያደክማል።

ከጥቂት ዓመታት በፊት በ1950ቹ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ስለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ያደረጉትን ንግግር ለዩኒቨርስቲ ተማሪዎቼ አንብቤላቸው "ይህን ማን የተናገረው ይመስላችኋል?" ብዬ ስጠይቃቸው ያለማቅማማት "መለስ ዜናዊ" ነበር ያሉኝ። "ፈጣን እድገት" የገጠሩ ሕዝባችን" "ኤክስቴንሽን ፕሮግራም" "ረሃብን ማስወገድ" "ኢንቬስትመንትን ማበረታታት" .... እነዚህና የመሳሰሉ አባባሎች ያኔ ተፈልስፈው አዲስ መጤው እንደገና ሲፈለስፋቸው የቆዩ ነገሮች ናቸው።

መንግሥቱ ኃይለ ማርያም አጼ ኃይለሥላሴን በማውገዝ ተነስቶ ወደኋላ የሳቸውኑ ሃሳቦች አንሻፎና አጣሞ ሊተገብራቸው ሞከረ። መለስም መንግሥቱን በማውገዝ ተነስቶ እነዚያኑ ሃሳቦች ይበልጥ አንሻፎና አጣሞ እየተገበራቸው ነው። በአለፉት ሃምሳ ዓመታት ውስጥ በለውጥ ሂደት ውስጥ ያለን ይምሰለን እንጂ እዚያው በዚያው እየዳከርን ነው። ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ!!!!

ከሁሉም በላይ አስገራሚው ነገር ደግሞ የለውጥ ተስፋ ሰጭ ሁኔታዎች ተፈጥረው በተበላሹ ቁጥር በርካታ የለውጡ አራማጆች ደንዝዘው የሚቀሩ መሆናቸው ነው። ብዙ ምሳሌዎችን ማንሳት ብችልም ሁለቱን ብቻ ልጥቀስ

- የ1966 አብዮት በጣም ተስፋ ሰጪ ነበር፤ ግን ተሰናከለ። ሌላ መንገድ ይኖር እንደሆን በመፈተሽ ፋንታ ቁጥራቸው ጥቂት የማይባል ምሁራን እስካሁንም እዚያው እንደቆሙ ናቸው። አንዳንዶቹ የ66ቱ ዓይነት አብዮት ዛሬም ሊመጣ ይችላል ብለው የሚያምኑ ይመስለኛል። "የካቲት 66 አልፏል፤ ተመልሶ ሊመጣ አይችልም። ጊዜው የተቀየረ በመሆኑ ቢመጣም አይጠቅመንም። ይልቁንስ ከዛ እጅግ የተሻለ ነገር ማምጣት እንችላለን" ብሎ ማሳመን ከባድ ነው።
- ሚያዝያ 30 1997 እፁብ ድንቅ ነበር፤ ግንቦት7 97ም ተዓምራዊ ነበር። እነዚህ በጉልበት ከተደፈጠጡ በኋላ አሁን ተመልሰው ይመጣሉ ብሎ ተስፋ ማድረግስ ያው የላይኛውን መድገም አይደለም? "ወንድሜ ይልቁንስ የጦር አዛዡ ሳሞራ የኑስ፤ የምርጫ ቦርዱ ኋላፊ ተስፋዬ መንገሻ፤ ከፍተኛ ፍ/ቤቱ ውስጥ መንበረ ፀሃይ ታደሰ ፈላጭ ቆራጭ ያልሆኑበት ሌላ ሚያዝያ 30 እና ሌላ ግንቦት7 እንፈልግ ስትሏቸው ,እምቢዮ .. እኔ የምፈልጋት .. የ97ዋን ሚያዝያ 30 እና የ97ዋን ግንቦት 7 ከነሰላማዊነታቸው ነው" ሲላችሁ ምን ታደርጋላችሁ? የሌለንና ሊኖር የማይችልን ነገር መመኘት!

ካጣናቸው መልካም ነገር የተሻሉ ሌሎች መልካም ነገሮችን መፍጠር የምንችል መሆኑን ባለመገንዘብ ወደፊት መሄድ አቅቶን አንድ ቦታ እንዳከርን ያለን ይመስለኛል።

ምንድነው ችግራችን? ለምድነው ወደፊት መሄድ ያልቻልነው? እነዚህ ጥያቄዎች ለመመለስ የአቅሜን ያህል ለፍቻለሁ። የተቻለኝን ያህል የኢትዮጵያን የቅርብ ጊዜ ታሪክ - በተለይም የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ታሪክን - ለማጥናት ሞክሬዓለሁ።

ለኔ የተሻለ ምላሽ ያገኘሁ ግን ፈጽሞ ካልጠበቅሁት ቦታ ነው - በአንድ በጥንቃቄ ከተፃፈች አጭር ትረካ። ብዙዎቻችሁ ትረካዋን ታውቋት ይሆናል። ቢሆንም እኔ አሳጥሬ እንዳወራት ፍቀዱልኝ።

ትረካው ውጥንቅጥ ውስጥ ስለገቡ አራት ትናንሽ ፍጥረቶች ነው። ስሞቻቸው ባህሪያቸውን እንዲወክሉ "ኤጭ"፣ "አሃ"፣ "ፈታሹ" እና "ፈጣኑ" ይሰኛሉ። አራቱም በጠዋት ተነስተው፤ በአጭር ታጥቀው በውጥንቅጡ ውስጥ የሚበላ ፍለጋ ይኳትኑ ነበር። ፍለጋቸው ውጤት አመጣና ለእያንዳንዳቸው እንደፍላጎታቸው ተስማሚ የሆነ አይብ በገፍ የተከማቸበትን ጣቢያ አገኙ። ጣቢያ ቁጥር 1 እንበለው።

ኤጭና አሃ እጃቸው ውስጥ በገባው ተዝቆ በማያልቅ ሃብት ተደሰቱ፣ ተዝናኑ። ችግርን ደህና ሰንብች አሏት። እንደቀድሞው በጠዋት መነሳቱን፣ በአጭር መታጠቁን እርግፍ አድርገው ተውት። "የለፋንበት ነው፤ የደከምንበት ነው" "ይገባናል!" ይላሉ። ፈታሹና ፈጣኑ ግን እንደቀድሞዓቸው በጠዋት ይነሳሉ፤ በአጭር ይታጠቃሉ፤ የከምቹቱን ዙርያ ይቃኛሉ፣ ያሸታሉ፣ ይለካሉ። ዓመታት አለፉ።

አንድ ቀን ረፋድ ላይ ኤጭና አሃ እንደልማዳቸው የጥንቱን ልፋታቸውና የአሁኑን ስኬታቸውን እያወጉ ወደ ጣቢያ ቁጥር 1 ሲገቡ ያዩትን ማመን አልቻሉም። አይቡ የለም!!!! ያ ተራራን ያህል የነበረው አይብ በቦታው የለም። ይህ እንዴት ይሆናል? ዓይኖቻቸውን አሻሽተው ፈተሿቸው። አንዳችም አይብ አይታይም። ያ ሁሉ አይብ የት ገባ? ማን ወሰደው? እንዴት ሊወሰድ ቻለ? ፈታሹና ፈጣኑ አለመኖራቸው ዘግይተው አስተዋሉ። እነሱ ወስደውት ይሆን? እንደምን ያንን ተራራ ችለው ያግዙታል? ምላሽ በሌላቸው ጥያቄዎች አዕምሮዓቸው ተበጠበጠ።

በማግስቱ ሁለቱ ሰዎች ወደ ጣቢያ ቁጥር 1 ሲያመሩ በሁለቱም ልብ ውስጥ ያ ይመኩበት የነበረው የአይብ ተራራ እንደሚጠብቃቸው ተስፋ አድርገው ነበር። ግን አልሆነም ጣቢያው ባዶ፣ ፍጹም ባዶ ነበር። በሶስተኛውም በአራተኛውም ቀንም አዲስ ነገር የለም። አሃ እየፈራ ኤጭን አናገረው .... "ስማማ ወንድሜ እኛው ያለማስተዋል ዝቀን ጨርሰነው ይሆን?... ታስታውሳለህ? ፈታሹና ፈጣኑ በየቀኑ አይባችንን ያሸቱና ይለኩ ነበር፤ ሲያልቅ ነጎዱ ... እኔና አንተ ግን ...."

ኤጭ በጩኸት አቋረጠው "የምትለውን ልሰማህ አልችልም!!! እነዚያን ደግሞ ስማቸውን አትጥራብኝ!!! ክልፍልፍ፣ አነፍናፊ፣ ፈታላዎች፣ ሰላቢዎች ... " እርግማን አወረደባቸው።

የሚቀጥሉት ቀናት በንትርክ አለፉ። አሃ በመቆየት የሚገኝ አንዳች ነገር እንደሌለ አምኗል ግና በማያውቀው ውጥንቅጥ ብቻውን መሄዱ አስፈርቶታል። ከኤጭ ጋር ከመጨቃጨቅ ስለ አዲስ የክምችት ጣብያ ማለም የተሻለ ሆኖ አገኘው። ይበልጥ ባለመ መጠን ደግሞ ይበልጡኑ እውነት እየመሰለው መጣ። የአዲሱ አይብ ውበት ይታየው፤ መዓዛው ያውደው ገባ። እይታው ግልጽ እየሆነ በመጣ ቁጥር በጣብያ ቁጥር 1 መቆየት ፋይዳ እንደሌለው ይሰማው ጀመር።

ኑሮ እየከፋ ተስፋቸው እየጨለመ መጣ። "ከግምቡ በስተጀርባ ተደብቆ ይሆናል እንጂ ያን የሚያህል አይብ ሊጠፋ አይችልም" አለ አንድ ቀን ኤጭ። በደከመ አቅማቸው ግንቡን ሠርስረው አዩ - እዚያም አይባቸው የለም።

አሃ በልፋትና በውጤት መካከል ስላለው ግኑኝነት ማሰላሰል ጀመረ። "ለፍተናል፣ ደክመናል ግን ውጤት አላመጣንም። ምናለ ይህንን ድካማችንን አይብ በሚያስገኝ ተግባር ላይ አውለነው ቢሆን ኖሮ ..... ይኬኔ እኮ አዲስ አይብ ለማግኘት ይኸን ያህል አያስለፋ ይሆናል ..." እያለ ያሰላስላል።

(ክፍል 2 ሳምንት ይቀጥላል)

# የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት

## ከኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን አገልግሎት የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ፣

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን አገልግሎት የተለያዩ፣ የዜና፣ የውይይት፣ ጥናታዊ፣ የመዝናኛ ፣ የስፖርት ፕሮግራሞቹን፣ በቀጥታ ወደ ኢትዮጵያ እና ወደ ሌሎች የአለም ክፍሎች በኤፕሪል መጭረሻ ማሰራጨት ይጀምራል።

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን አገልግሎት ያቋቋምን አካላት ኢትዮጵያ ሀገራችን እና ህዝቧ አሁን ለሚገኙበት እጅግ አስቸጋሪ እና ውስብስብ ሁኔታ ውስጥ እንዲደርሱ ከአደረጓቸው በርካታ ምክንያቶች አንዱ እና ዋናው፣ ለረጅም ዘመን ህዝቡ ስለ እራሱ እና በጋራ ስለሚኖርባት ሀገር ስለሚገኙበት ሁኔታ፣ ትክከለኛውን መረጃ በአይነትም ሆነ በመጠን ማግኘት አለመቻሉ ነው ብለን እናምናለን።

ሀገራችን ኢትዮጵያ እና ህዝቧ ዛሬ ለሚገኙበት እጂግ አስቸጋሪ እና ውስብስብ ችግሮች በተመለከተ መፍትሄ መፈለግ አለብን ብሎ ከልቡ የሚያስብ ዜጋ በሙሉ፣ ህዝብ ሁለንተናዊ ጉዳዮች ላይ ትክክለኛ መረጃ ማግኘት፣ በአገኛቸውም መረጃዎች ላይ ተመስርቶ በጋራ በመምከር፣ የጋራ መፍተሄ ማፈላለግ፣ ብሎም ለመፍትሄው ተግባራዊነት በጋር ለመንቀሳቀስ የሚችለው፣ ነጻ እና አስተማማኝ የመረጃ ምንጭ ሲኖር ብቻ መሆኑን መቀበል ያስፈልጋል።

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን አገልግሎት የህዝብ ዓይን እና ጆሮ፣ የመገናኛ ብዙሀን በመሆን፣ አስተማማኝ ነጻ እና ገለልተኛ መረጃዎችን በማቅረብ፣ ለችግሮቻችን መፍተሄ ለመፈለግ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የራሱን አስተዋጽዖ ለማድረግ ዝግጁ ሆኖ ቀርቧል።

የጋራ ችግሮቻችን መፍትሄ ያገኙ ዘንድ ከጋራ ጥረት ውጭ ሌላ አማራጭ የለንም ። በጋራ ጥረት ለማድረግ ደግሞ በጋራ ሊያስማሙን የሚችሉ ጉዳዮች ሊኖሩን ይገባል። የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን አገልግሎት የሚቀርቡ ፕሮጋራሞች በሙሉ ሁላችንንም በጋራ ሊያስማሙን ከሚችሉት የእውነት፣ የሚዛናዊነት፣ የግጽነት እና የተጠያቂነት መመዘኛዎችን ያሟሉ መሆን ይኖርባቸዋል። እነዚህን መመዘኛዎች ሳያሟሉ ቢቀሩ ግን፣ ሀገራችንን እና ህዝቧን ለዘመናት ተብትቦ ወደ አዘቅት እያወረደን ካለው የጥቂት ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ጉዳይ ማስተናገጃ መድረክ ከመሆን አዙሪት መውጣት ስለማንችል፣ ጥረታችን ሁሉ ከንቱ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን አገልግሎትን ያቋቋምን ወገኖች ይህንን ከፍተኛ የግንዛቤ፣ የእቅድ፣ የገንዘብ እና የማቴሪያል፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ይቻላል የሚል የመንፈስ ጽናት፣ የሚጠይቅ ጥረት፣ በጥቂት ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ከታሰበለት ግብ ማድረስ ይቻላል የሚል እምነት የለንም። ይህ ጥረት በተወሰኑ ሰዎች ይጀመር እንጂ፣ የታሰበለትን ዓላማ ተግባራዊ ለማድረግ ሁላችንንም በምንችለው ሁሉ እስተዋጽዖ ማድረግ ይኖርብናል። ይህ እስተዋጽዖ የማበረታቻ የሀሳብ ድጋፍ ጀምሮ በሙያ እና በገንዘብ ድረስ የሚደርስ ድጋፍ ሊሆን ይገባል።

በዚህ ሀገራዊ እና ህዝባዊ ጥረት ማንም ገለልተኛ መሆን ስለማይገባው ሁላችንም በምንችለው ሁሉ እንድንሳተፍ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

### የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን አገልግሎት ድርጅት፣

ኢሳትን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃዎችን ወይም ቃለመጠየቅ በማድረግ ቢያንስ የአማካሪ ቦርድ ቃል አቀባይ የሆኑትን አቶ አበበ በለውን በስልክ ቁጥር +1244724439 ወይም በኢሜል abelewd@yahoo.com ወይም ማኔጂንግ ኤዲተር አ ቶ ፋሲል የኔአለምን በ0031 455 112993 ወይም በኢሜል bikoetht@gmail.com ማግኘት ይችላሉ።

ኤፕሪል 2010 ዓ.ም

www.ethsat.com

## ዜጎችን በሙስና እንዲዘፈቁ ማበረታታት ከወያኔ የቁጥጥር ዘዴዎች አንዱ ነው ተባለ

የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ከምርጫ 97 ሽንፈቱ በኋላ የኢትዮጵያን ህዝብ በሁሉም አቅጣጫ ለመቆጣጠር ካወጣቸው እቅዶች ውስጥ አንዱ በማህበረሰቡ ውስጥ ተጽእኖ እንዳላቸው የሚገመቱ ዜጎች በሙስና እንዲዘፈቁ ማበረታታት መሆኑን አንድ የፖለቲካ ተንታኝ ለግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ገለጹ።

ዘጋቢያችን በተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች ከሚኖሩና በተለይም ወደ ሃይማኖት ተቋማት ቅርብ ከሆኑ ዜጎች ጋር በመነጋገር እንዳሰባሰበችው መረጃ፣ በምርጫ 97 ወቅት አገዛዙን ክፉኛ ይቃወሙ የነበሩ የቤተ-እምነቶች አገልጋዮች በተለያዩ የሙስና ወጥመዶች ውስጥ ወድቀዋል።

የወያኔን ኢ-ፍትሃዊ አሰራር አምርረው ይቃወሙ የነበሩ አንዳንድ የቤተ-ክርስቲያን አገልጋዮች፣ ህገ-ወጥ የመሬት ንግድ ውስጥ ገብተው ሃብት ለማጋበስ ከቻሉ በኋላ ግን አንዳንዶቹ ዝምተኛነትን ሲመርጡ የተቀሩት በግልጽ ወያኔን መደገፍ እንደጀመሩ ዘጋቢያችን ያሰባሰበቻቸው ምሳሌዎች ያስረዳሉ።

ከተለያዩ ምንጮች የተሰባሰቡት መረጃዎች እንደሚያሳዩት ከሆነ እንዲህ አይነቱ ሙስና እጅግ ተስፋፍቷል። በየከተሞች እና መንደሮች፤ እንዲሁም በሃይማኖት ተቋማት ውስጥ ተጽእኖ አላቸው ተብለው የሚገመቱ ብዙ ዜጎች የሚሰሩትን ስራ ህገ-ወጥነት ባለማስተዋል፣ ወይም ጉዳይ ባለመስጠት በሙስና ውስጥ ለመዘፈቅ መብቃታቸው ታውቋል።

ዘጋቢያችን በዚህ ጉዳይ ላይ ያነጋገረቻቸው የፖለቲካ ተንታኝ፥ እንዲህ አይነቱ አሰራር በአምባገነን አገዛዞች ዘንድ አዲስ እንዳልሆነ ጠቅሰው፣ እነዚህ ሰዎች ወንጀል ከፈጸሙ ሊነሱብኝ አይችሉም ከሚል እና ቢነሱም ማስፈራሪያ እና እስር ቤት መከተቻ የሚሆን በቂ ምክንያት ይኖራል ከሚል ስሌት የተነሳ እንደሆነ ገልጸዋል።

## ኩማ ደመቅሳ የኪነ-ጥበብ ሰዎች ወያኔን የሚያሞጋግሱ ስራዎችን እንዲሰሩ አዘዘ

የአዲስ አበባ ከተማን እንዲያስተዳድር ወያኔ የሾመው ኩማ ደመቅሳ፣ ሰሞኑን የኪነ-ጥበብ ሰዎችን ሰብስቦ ማህበረሰቡን በማነቃቃት ያለባቸውን፣ እንደሱ አገላለጽ "ልማታዊ ሃላፊነት"፣ ባለመወጣት እንዳወገዛቸው የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከው ዘገባ አስታውቋል።

የኪነ-ጥበብ ሰዎች በሁሉም አቅጣጫ ወያኔ አገሪቱን ለመገንባት የሰራቸውን ጥሩ ነገሮች ለማህበረሰቡ በማሳወቅ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉም ትእዛዝ አስተላልፏል።

የስብሰባው ተካፋዮች ከነበሩት ውስጥ ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው አርቲስቶች፥ ያለው ረሃብ፣ የመልካም አስተዳደር ጉድለት እና ሙስና ሆኖ ሳለ ምን ይዘው እንዲያሞግሱ እንደተፈለገ እንዳልገባቸው በመናገር በኩማ ትእዛዝ ላይ መሳለቃቸው ታውቋል።

## የእስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት . . . ከገጽ 1 የቀጠለ

እንዳይወጡ ለማድረግ የታቀደ የወያኔ ሴራ እንደሆነና ውሳኔውን ወደ ጎን ትተው ያሻቸውን እንደሚያደርጉ ለዘጋቢያችን ገልጸዋል።

የወያኔ አገዛዝ የስልጣን ዘመኑን ለማራዘም በሚያደርገው ሩጫ ሃይማኖታዊ ተቋማትን መቆጣጠር አንዱ አላማው በመሆኑ፤ ተቋማቱን በሙስና በተሳሰራቸው ሃላፊዎች በመሙላት ቤተ-እምነቶችን እያረከሰ እንደሆነ በተደጋጋሚ ዘገባዎቻችን ማሳየታችን ይታወሳል።


### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ
### የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

**በ 7530 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ** እና **በ 9610 KHZ በ 31 ሜትር ባንድ** ላይ የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን g7radio@ginbot7.org ወይም በስልክ ቁጥር 0044- 203-286- 9661